“ሀገር ማለት የኔ ልጅ!”

(በዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ)

ሀገር ማለት ልጄ፣

ሀገር ማለት፣

እንዳይመስልሽ የተወለድሽበት ቦታ፣የተወለድሽበት አፈር፤

እትብትሽ የተቀበረበት፣ቀድመሽ የተነፈሽው አየር፤

ብቻ እንዳይመስልሽ።

ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ፤

አገር ውስብስብ ነው ውሉ።

ሀገር ማለት ልጄ፣

ሀገር ማለት ምስል ነው፣በህሊና የምታኖሪው፤

ከማማ መህጸን ከወጣሽበት ቀን ጀምሮ፤

በጠባሽው ጡት፣ወይም ጡጦ፣

በዳህሽበት ደጃፍ፣በወደቅሽበት ፈፋ፤

በተማርሽበት ትምህርት ቤት፣

በተሻገርሽው ኧርፈት፤

በተሳልሽበት ታቦት፣ወይ በተማፀንሽው ከራማ፤

በእውቀትሽና በህይወትሽ፣

በእውነትሽና በስሜትሽ፣

የምትቀበይው ምስል ነው፣በህሊናሽ የምታኖሪው፤

ስትወጅ ሰንደቅ ታደርጊው።

ቢያስጠላሽ የማትቀይሪው።

ደራሲ አስራት አብርሃም ሀገርማለት የኔልጅ፣

ሀገር ማለት ቋንቋ ነው በአንደበት አይናገሩት፤

በጆሮ አያዳምጡት፤

አማርኛ ኦሮሞኛ፣አፋርኛ ቅማንተኛ፤

ጉራግኛ ወይ ትግርኛ፣ብለው የማይፈርጁት።

የኔ ልጅ፣

አማራውና አፋሩ፣ኦሮሞው ሲዳማው፣ጉራጌኛሽን ባይሰማ፤

ያለገባው እንዳይመስልሽ፣ሀዘን ደስታሽን ያልተጋራ።

የየልቦናችንን ሀቅ፣ፍንትው አድርጎ እያሳየ፤

ህዝቦችን ከሰንደቃቸው፣አስተሳስሮ ያቆየ።

ሀገር ቋንቋ ነው ልጄ፣የሁለንተናሽ መስታወት፤

ሲከፋሽ ትሸሸጊበት፣ሲደላሽ ትኳኳየዪበት።

የኔ ልጅ፣

አያት ቅምአያትሽ፣ሰላም ሲሆን ከወልቂጤ አድማስ ማዶ ሸቅጦ፣

ሲያቀና ወረቱን፤

ለእኔና ለአንቺ መኖሪያ፣ሲያቀና ቀዬና ቤቱን፤

ሀገር ጠላት ሲደፍራትም፣ጦሩን ሰብቆ እየፎከረ፤

ከኦሮሞው ከትግሬው፣ከአፋሩ ከወላይታው፣ . . . ከሁሉም የጦቢያ ልጆች፣

አጥንቱን እየማገረ፤

ሀገር ይሉት መግባቢያ፣ሰንደቅ ይሉት መለያ፣ሲያቆይልሽ፤

በጉራግኛ ማትገልጭው፣በጎጥ የማትገድቢው፣ስንት አለ ታሪክ መሰለሽ!

እና የእኔ ልጅ፣

ለዚህ ነው ሀገር ይሉት ቋንቋ፣ላንቺ የሚያስፈልግሽ፤

ከወልቂጤ አድማስ ማዶ፣ለተሳሰረ ታሪክሽ፤

ከወልቂጤ አድማስ ማዶ፣ለተወጠነው እድገትሽ።

እና ልብበይ ልጄ ! ሀገር ማለት ቋንቋ ነው፣ባንደበት አይናገሩት፤

በጆሮ አያዳምጡት።።

ከሁሉም በላይ ልጄ፣

ተፈጥሮ ከቸረው በረከት፣የላቡን ፍሬ የሚበላ፤

ሀገር ማለት ወገን ነው፣የእኔ የምትይው ከለላ።።

ትመኪበት ጥሪት፣ትደምቂበት ብርሃንሽ፤

የሰብዕናሽ ግማሽ ውል፣ወገን ነው ማሕተምሽ።።

ዜጋው ነው ልጄ ሀገርሽ።።

መሬትማ የእኔ ልጅ፣

በእምነትሽና እውቀትሽ፣ከልለሽ ካላበጀሽው፤

ለእድገትሽ ውጥን ካልሆነ፣ለተስፋሽ ካልተመገብሽው፤

መሬትማ ባዳ ነው፣ላለማው የሚለማ፤

ለተስማማው የሚስማማ።።

ኸርቱም ግድ የለውም፣ቦይ ለማሰለት ይፈሳል

ተራራውም ደንቆሮ ነው፣ለቦረቦረው ይበሳል።።

መሬቱአደለም የኔ ልጅ፣እድርተኛው ነው ሃገርሽ፤

ስትቸገሪ ታድጎ፣ስትታመሚ አስታሞ፣ስትሞቺ አፈር ሚያለብስሽ።።

በእጅሽ ያለ ብሩህ ጽጌ፣ሰው ነው ልጄ ሀገርሽ፤

ወገን ነው ልጄ ሀገርሽ።።

እና የኔ ልጅ፣

ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ፤

ሀገር ውስብስብ ነው ውሉ።።